እርማችሁን አውጡ !!

የሽልንግ ዶሮ የብር ገመድ ይዛ ጠፋች

ያኔ በደጉ ዘመን መሆኑ ነዉ፤ አስር እንቁላል በአስር ሳንቲም፤ አንድ ጠቦት በሶስት ብር ፤ አንድ የሰባ ሰንጋ በአስር ብር ፤ ወዘተረፈ ...ሲቸበቸብ ዶሮ ፈላጊዋ በዝቶ ዋጋ ዋናረና ሕዝቡ ለንጉሰ ነገስቱ እንዲህ ብሎ አቤቱታዉን አሰማ አሉ( ሀይሌ ማረኝ ማረኝ ፤ ሐይሌ ማረኝ ማረኝ ዶሮ ብር አወጣች እኔስ ጋ አማረኝ) ከዛ በኋላ ማየጎዝብ ቁጥር እየገፋ ከተሜዉ እየደረጀና እየሰፋ ሲመጣ እንኳን አዲሱ ትዉልድ ሞፈር ቀንበር ጨብጦ ሕዝብ ሊያጠግብ ቀርቶ ነባሩም ገበሬ ቀለም ቆጥሮ ዘመነኛ ለመሆን እና ፀዳ ያለ ኑሮ ለመኖር ከገጠር ይልቅ የከተሜዉን ሕይወት ይናፍቅ ጀመር ። በዚህ አይነት የአርሶ አደሩና የአርብቶ አደሩ ሚና ዉስን ሖኖ ኑሮ ጣራ ነካ ። ይህን የተገነዘቡ አንድ እናት ቀደም ብለዉ በሽልን የገዟትን ገብስማ ዶሮ አይን አይኗን እያዩ እንቁላሏን እንጂ እርሷን አርደዉ መመገብ አልደፈሩም። እንዲያዉም በነፃነት የመንቀሳቀስ መብቷን ገድበዉ በክት መቀነታቸዉ በማሰር ጠሬ ይቀልቧት ጀመር ።

ዶሮዋ ግን ብዙ አለቆየችም አንድን ጋት ከአይን ተሰወረች። እንኳን ዶሮዋ በሁለት ሽልንግ ተገስቶ እግሯን የሸበበዉ መቀነታቸዉ ደብዛዉ ጠፋ። ከሁለት አንዱንም አጡ( የሽልንግ ዶሮ የብር ገመድ የተባለዉ እንዲህ ነዉ)። ኋላማ ሐዘን በልባቸዉ ገብቶ እርማቸዉን አወጡ፤ ፆሙንም ገፉበት።

እኛስ ከዚች ዶሮ ተምሳሌትና ከወይዘሮዋ የህይወት ገጠመኝ ተምረን ለምን እርማችንን አናወጣም? ለምን ዉሸን ያነሳ ዉሸ ይሁን ፤ ኳሷን ያነሳ ኳሶ ይሁን አልንም? ከአንድ አመት በላይ በቃላት ጋጋታ እዉነትን ለማድበስበስ ከመጣር ይልቅ ለምን በይቅርታ መስጠትና መቀበል አናምንም? “ ከሰዉ ስህተት ከብረት ዝገት” የሚለዉን ጥቅስ መማማሪያ ከማድረግ ይልቅ ዛሬም በዛ ገጉሮሮ የዛገ ቃላትን መደርደሩ ምን ይፈይዳል? ገና ከጂምሩ ገመና በዚህ ዙሪያ ና በጁላይ 2010 አምስተርዳም ላይ የተካሔደዉን የኳስ ተስካር አስመልክቶ ብዙ ብሏል። በወቅቱ የተካሕደዉን ትእይንት ለሕዝብ አስነብቧል። የተደበቁ እዉነታዎችን ገሐድ አዉጥቷል፡ ሕዝቡ በጉዳዩ አንዲወያይ መድረክ ፈጥሯል፤ ሁኔታዉ በወገን ችሎት እንዲታይ ግፊት አሳድሯል፡ ወዘተ... እናስ ዛሬስ የገመና ቃል ያጠራጥርዎታልን ?

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ከዚህ ቀደም በአራት ክፍሎች በመከፈል የተደረደሩት እዉነተኛ የገመና ድርሰቶች እጅግ የብዙ አንባቢያንን ቀልብ የሳቡና ትምሕርት ሰጭነታቸዉ የጎላ መሆኑን የዚህ ፅሁፍ ባለቤት እስከዛሬ ከደረሱት በርካታ የሕዝብ አስተያየቶች አረጋግጧል። ዛሬ ደግሞ ገመና በክፍል አምስት መጣጥፉ ከአንድ አመት በላይ ሲጠበቅ የነበረዉን እና በሴፐቴምበር 28 2011 ይፋ የሆነዉን የኦዲተሮች የሒሳብ ምርመራ ዉጤት አባሪ አድርጎ በማሳየት የራሱን አስተያየት አክሎበት ያስነብበዎታል።

ላለፉት ስድስት ወራት ያሕል ለሁለተኛ ግዜ በተዋቀሩት አምስቱ የኦዲት ኮሚቴዎች ተይዞ የነበረዉ ምርመራ ሐቀኝነትን ፤ ቆራጠኝነትን ፤ ሚዛናዊነትን ና ፤ አስተዋይነትን የሚጠይቅ ለመሆኑ አጠያያቂነት የለዉም። በዚህ ረገድ የኦዲት ኮሚቴ አባላቶች ጉዳዩን ይፋ ለማድረግ ያደረጉት ጥረት የሚያስመሰግናቸዉ ሲሆን አስተያየት የሚጠይቁ ነገሮችን ወደኋላ እጠቅሳለዉ። በዚህ የማጣራት ሂደት ዘጠኝ አባላት የሚገኙበት የ2010 የአምስተርዳሙ የባእል አዘጋጅ

ሆኖ አልፏል። ይህ ብቻም አይደለም፤ በጥቂት የአጋጅ ኮሚቴ አባላቶች እና መልእክተኞቻቸዉ ቤት ስራ የአብዛኛዉ

ኳስተጫዋቾች የእርስበርስ ወንድማዊ ትስስር ገመድ ተበጥሷል፤ ይህንን ሆን ተብሎ የታቀደ ትእይንት ያጋለጡና

የነቀፉ ግለሰቦች ስማቸዉ ጠፍቷል።

እንግዲህ እንዲህ አይነቱን ተዉኔት በዝምታ እንድናይ ያስገደደን እና በግዜዉ ሆዳችንን ያባባን አንድ በአዘጋጅ

ኮሚቴ በኩል የተለፈፈ ቁም ነገር መሰል ማፌዣመፈክር ነበር ይኸዉም... ከዝግጅቱ ከሚገኘዉ ትርፍ የሕፃናትና

የወጣቶች መሰብሰቢያ አደራሽ ይገነባል፤ ይታነፃል፤ የገዛል፤ ይከራያል፤ ይመራል ወዘተ... “ፅድቁ ቀርቶ በወጉ

በኮነነኝ አሉ” ያምናሰዎች። ሕብረተሰቡ ግዜናገንዘቡን ፤ ማህበሩ ቢሮና መርገጫ ማሕተሙን በመስጠት የተከናወነዉ

ድግስ እንኳን መዝናኛ አዳራሽ ሊገዛ ቀርቶ ቁርጡን ንገሩን አትንገሩን በሚል በጓዳዉ ኮሪደር ላይ እሰጥአገባዉ

በርክቷል ይባላል። የባህል አዘጋጅ ኮሚቴዉ ባመጣዉ ዳፋ የአምስተር ዳሙ መዘጋጃ ቤት የ28 አመቱን ማሕበር እድሜ

ሊያሳጥር የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ መላኩን የኦዲት ዘገባዉ አትቷል።

አንግዲህ ኳስና ድግሱ ባመጣዉ ጣጣ ከላይ የታዩት ችግሮች እንዳሉ ሆነዉ ከደረሰዉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ክስረት

የሽልንግ ዶሮ ተረት ለኛ አነሰንትላላችሁ?

ማጠቃለያ ፡ ይህ የገመና ጥንቅር በ 28-09-2011 በኢትዮጵያ ማሕበር ኮሪደር የተደመጠዉና የተበተነዉን

የኦዲተሮች ዘገባ የተንተራሰ ነው። ሆኖም የባህል አዘጋጅ ኮሚቴዉ በጠየቀዉ ይግባኝ መሰረት ሁኔታዉን በጥቂቱ

ለመመልከት የኦዲት ኮሚቴዉ ድጋሚ ቀጠሮ ይዟል፤ በመሆኑ ምገመና የሚቀጥለዉ ወሳኝ ቀጠሮ ላይ ሕ/ሰቡ ትኩረት ሰጦ

በአዘጋጅ ኮሚቴዎች እጅ አለየተባለዉ ገንዘብ እንዲመለስና ጥቂት የተባሉት የባእል አዘጋጅ ኮሚቴዎች

አድራጎታቸዉን በማመን ይቅርታ ጥያቄ ላይ እንዲደርሱ ግፊት ማድረግ ይገባል ሲል ደምድሟል።

# በአምስተርዳም 8ኛው አውሮጳ አቀፍ

# የስፖርትና ባህል ፌስቲቫል 2010

## የኦዲት ሪፖርት

ኦክቶበር 2011

አምስተርዳም

October 2, 2011

## የኦዲት ኮሚቴ የስራ ዘገባ

በ17.04.2011 የኢትዮጵያ ማህበር አምስተርዳም ቅርንጫፍ በጠራው ጠቅላላ ጉባዔ በህዝብ ውክልና የተሰጠው አምስት አባላት ያሉት የኦዲት ኮሜቴ መመረጡ ይታወሳል። የተመረጥነውም የኦዲት ኮሚቴው አባላት በተለያዩ ምክንያት ምርመራው ተጠናቆ ለህዝብ ይፋ ያልሆነውን የ8ኛውን አውሮጳ አቀፍ የስፖርትና ባህል ፌስቲቫል አዘጋጅ ኮሚቴ ስራ መርምረን ለጠ/ጉባዔው እንድናቀርብ ሀላፊነት ተሰጥቶናል።

በዚሁም መሰረት ከዚህ በታች ጠቅላላ የኮሚቴውን የስራ ሂደት፣ ወጭና ገቢውን ምርመራ ውጤት እናቀርባለን።.

| | |
|---|---|
| የኮሚቴው ስም | የአምስተርዳም ስፖርት ፌስቲቫል በዓል አዘጋጅ ኮሚቴ |
| የስራ ዘመን | ከሴፐተምበር 2010 እስከ ዝግጅቱ ፍፃሜ (ዲሴምበር 2010) |
| የዝግጅት ቦታ | አምስተርዳም |
| የአባላት ብዛት | 9 በህዝብ የተመረጡ የኮሚቴ አባላት። |

ኮሚቴው ከዝግጅቱ በሚገኘው ገቢ ለማህበረሰቡ አባላት የሚያገለግል ሁለገብ የጋራ መገልገያ ተቋም መከራየት ወይም መግዛት ዋና ግቡ መሆኑን በይፋ በማሳወቅ ስራውን ጀምሯል።

ለዚህ ዓላማው ግብ መምታት ይረዳው ዘንድ የወልና የግል ሀላፊነትን በሚመለከት መመሪያ አውጥቷል።ዝርዝር የኮሚቴውን የስራ ሀላፊነትና አፈጻፀማቸውን በተለያዩ አንቀጾች ላይ አስፍሯል። የኮሚቴው የስራ ዘመንና ተግባር ከዝግጅቱ ጋር ብቻ የተያያዘ መሆኑን በመግለፅ ተጠያቂነቱም ለአምስተርዳም ማህበር፣ ጠቅላላ ጉባዔ መሆኑን አሳውቋል።

### ሀ.የበዓል አዘጋጅ ኮሚቴው ዋና ዓላማ

በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ ሀ በተጠቀሰው መሰረት የአዘጋጅ ኮሚቴው በአምስተርዳም ከተማ የሚዘጋጀው 8ኛው አውሮጳ ዓቀፍ የኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ፌስቲቫል የተሳካ ይሆን ዘንድ

- ስፖርታዊ ውድድሮችን ማከናወን
- ከተለያዩ አለማት የሚመጡ ኢትዮጵያውያንን ማገናኘት
- የሀገራችንን ባህልና የስፖርት ጥንካሬ ለምንኖርበት ህብረተሰብ ማስተዋወቅ
- የስፖርት ኮሚቴውን ለማጠናከርና አንድ ማዕከል ለማቋቋም
- 'በአባላት መካከል ጤናማ ግንኙነት ለመፍጠርና ማህበራችንን ለማጠናከር

### ለ.የኮሚቴው ተግባር

ከላይ የተገለፀውን ዓላማ እውን ያደርግ ዘንድ የበዓል አዘጋጅ ኮሚቴው የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

- ዓላማውን ተግባራዊ ያደርግ ዘንድ እቅድ ማውጣትና አመራር መስጠት
- ለጠቅላላ ዝግጅቱ ስራ ማስኬጃ የሚሆን ገንዘብ ማፈላለግ
- የተለያዩ ስራዎችን የሚያስተባብሩ ንዑሳን ኮሚቴ አባላትን፣ከስፖርት ቤተሰብና ከማህበረሰቡ አባላት መካከል መሰየምና ስራቸውን መከታተል
- የስፖርት ቤተሰቡም ሆነ የማህበረሰቡ አባላት በበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት እንዲሳተፉ ጥሪ ማድረግና እንዲሳተፉ ማበረታት

### ሐ. ተጠሪነት

ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለጠቅላላው የኢትዮጵያውያን ማህበር ጠ/ጉባዔ ይሆናል። ከማህበሩና ከስፖርት ኮሚቴው ጋር የጠበቀ የስራ ግንኙነት ይኖረዋል።

## መ. የኮሚቴው አባላት

1. አቶ ለገሰ ቱጂ ሰብሳቢ
2. አቶ ተፈራ ዘርፉ ም/ሰብሳቢ
3. አቶ ሀይማኖት ውዱ ዋና ፀሀፊ
4. ወ/ሮ ዓለም ደስታ ረ/ፀሀፊ
5. አቶ ዘሪሁን ሽጉጤ ገንዘብ ያዥ
6. አቶ ክንፉ አሰፋ ህ/ግንኙነት
7. አቶ ዘውዴ ከበደ አባል
8. አቶ የሱፍ ገደፋው አባል
9. አቶ በላይ አበበ አባል

## ሠ. የኦዲት ኮሚቴ አባላት

1ኛ. አቶ ካሳሁን ዓሊ ሰብሳቢ
2ኛ. አቶ ዳዊት ደሱ ፀሀፊ
3ኛ. አቶ ሚኒልክ ወ/ጊ. አባል
4ኛ. አቶ ቢሳይ ገ/ልዑል አባል
5ኛ. አቶ የሱፍ ገደፋው አባል

## ረ. የኦዲት ተግባር

የበዓል አዘጋጅ ኮሚቴው ስራውን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያከናወነውን ተግባራት መርምሮ ውጤቱን ለጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ።
በሥራው ሂደት ጉድለት ተፈጥሮ ከተገኘ ከተፈጠረው ስህተት ትምህርት ወስዶ ወደፊት ተመሳሳይ ግድፈት እንዳይደገም እርምት እንዲደረግ የሚመለከታቸውን ሁሉ ለማስገንዘብና ተጠያቂነት መሆኑንም ጭምር እንዲያውቁ ለማድረግ።
በጎ ጎኑንም በማየትና በመመርመር እንዲበረታታ ማድረግ።

## ሰ- በኦዲት ኮሚቴ ቅድመ ምርመራ የተከናዎኑ ሥራዎች፤

የኦዲት ኮሚቴው ከ10 ያላነሱ መደበኛ ስብሰባዎች በማድረግ፤

- የበአል አዘጋጅ ኮሚቴ አባላትን በወቅቱ ስለነበራቸው የሥራ ድርሻና ሃላፊነት፤
- ስለ ክብር እንግዳና ዘፋኞች አመራረጥ፣
- ስለ ሰው ሀይል ምልመላና ክፍያ አፈፃፀም
- ስለ ሰነድ አያያዝና ገንዘብ አጠቃቀም ጥያቄ አቅርበንላቸዋል።
  - በእጃቸው የሚገኘውን ማንኛውም ዓይነት ሰነድ ዋናውን (ኦርጅናሉን)
  - የቃለ ጉባኤ መዝገብ
  - የውሳኔ ስምምነት ሰነድ
  - ግዥና ክፍያ የተፈፀመባቸው ደረሰኞች
  - የውል ስምምነት ሰነዶች
  - የሞዴል ሾው የመግቢያ ቲኬት፣ የሙዚቃ ምሽት የመግቢያ ቲኬትና የፓርኪንግ ገቢ መሰብሰቢያ ትኬት ለምርመራው ሂደት እንዲረዳን እንዲሰጡን ጠይቀናቸዋል።
  - በቋሚነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ንብረቶች ካሉ እንዲያሳውቁን ጠይቀናል።

በዚህም መሠረት ቀደም ሲል በስራው ላይ ለነበሩት ለኮሚቴ አባላት ለቀረቡት የተለያዩ ጥያቄዎች; አቶ ተፈራ፣አቶ ክንፉና አቶ ለገሰ ለዝግጅቱ ስራ ከተመረጡት ዘጠኝ የኮሚቴ አባላት ውስጥ ራሳቸውን ያገለሉ በመሆናቸውና ፈቃደኛ ሆነው ከተመዘገቡት ሰዎች መካከል የተገኙት ጥቂት ሰዎች ብቻ በመሆናቸው ሥራው እንዳይበደል፣የዝግጅቱ ወቅትም በመቃረቡ መተዳደሪያ ደንቡ ከሚፈቅደው የሥራ ድርሻና ድልድል ውጪ ሥራውን ለመሥራት መገደዳቸውን፣እንዲሁም የሰው ሀይል ምደባንና ክፍያን አስመልክተው የስራ ዘርፉና የሰው ሀይል አስፈላጊነት ብዙ በመሆኑና በፈቃደኝነት ለማገልገል ቃል የገቡ~~ትም~~ ባለመምጣታቸው ጫናም ሰለበዛብን ምንም አማራጭ ስሌሌለን በወቅቱ ያገኘናቸውንና በክፍያ ሊሰሩ ፈቃደኛ የሆኑትን በጠየቁት ክፍያ መሰረት ለማሰራት መስማማታቸውን ተናግረዋል።

የቲኬቶቹን ብዛትና አሻሻጥ እንደሚከተለው አቅርበናል።

| | ጠቅላላ( ቅጠሎች) | የተሸጠ | ተመላሽ | ውድቅ የተደረገ |
|---|---|---|---|---|
| ከአቶ ደበበ | 50 | 31 | 19 | |
| እስራኤል | 500 | 481 | 19 | 8 ትኬቶች ተጎርደው በተመላሽነት የቀረበ |
| ኢበላ ሬስቶራንት 16 | 50 | 34 | 16 (15*) | |
| አድስ አበባ 38 | 50 | 12 | 38 | |
| አቡማ ዳንኤል 6 | 600 | 590 | 10 | |
| በቦጋለ 34 | 500 | **464** *** | 36 | 8 ትኬቶች ተጎርደው በተመላሽነት የቀረበ<br>195 ቲኬቶች ፍንጫቸው የጠፋ |

2500 ጠቅላላ ቅጠሎች (ቲኬቶች)

1612 ቲኬቶች ተሸጠዋል
138 ተመላሽ ቲኬቶች
750 በኮሚቴው እጅ የሚገኝ